# በኢትዮጵያ የመፈንቅለ መንግሥት ይዘት ያለው ወታደራዊ አገዛዝ ሊታወጅ ነው!

www.goolgule.com/ethiopia-to-be-under-a-total-military-rule/

Editor




በኢትዮጵያ በተከታታይ የዘለቀውን ሕዝባዊ ተቃውሞ መቆጣጠር የተሳነው ህወሓት በኢትዮጵያ በአስቸኳይ አዋጅ ስም አገሪቷን በወታደራዊ አስተዳደር ስር ለማስተዳደር ኣዋጅ እንደሚያወጣ ተሰማ። የመፈንቅለ መንግሥት ይዘት ያለው አዋጅ ምናልባትም ዛሬ ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል።

- ያለፈው የኢህአዴግ ስብሰባ ወቅት ስምምነት ተደርሶበት የነበረው ሁሉንም ያሳተፈ የሽግግር መንግስት ምስረታ ህወሓት ኣልቀበለውም ብሏል፥
- ይህንን ተከትሉ ሃይለማርያም ደሳለኝ ከስልጣኑ እንዲወርድ በህወሓት ግፊት ሲደረግበት ቆይቷል፤
- የሃይለማርያም በፈቃዱ ከስልጣን መውረድ ለህወሓት የደኢህዴንን ስጋት እንዲቀንስለት ታስቦ የተደረገ ግፊት ነው፥
- የኦህዴድ መከዳትና የብአዴን መከተል ላይ ደኢህዴን ከተጨመረ የህወሓትን ህልውና አደጋ ላይ መጣሉ ስላሰጋው ነው ህወሓት ሃይለማርያም በፈቃዱ ለቀቀ ማስባል የፈለገው፥
- ወታደራዊ አገዛዝ ከታወጀ በኋላ ህወሓት ያለ ርህራሄ ማንኛውንም ተቃውሞ "የመጨረሻ ውሳኔ" በማስተላለፍ ታይቶ የማይታወቅ ደም ማፋሰስ በአገሪታ ላይ በማስከተል ስልጣኑን ለማረጋጋት የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል፤
- ይህንን ተፈጻሚ ለማድረግና ከጌቶቹ ፈቃድ ለማግኘት በኦሮሞ ስም ለትግራይ የሚጫወተው ወርቅነህ ገበየሁ ነገዎ/ወልደጻድቅ አሜሪካ ይገኛል፥
- ጎልጉል የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው በአሜሪካኖቹ በኩል ሙሉ ስምምነት ባይኖርም አንዳንዶቹ ግን "የአሜሪካንን ጥቅም የሚያስጠብቁት ትግሬዎች ናቸው" በማለት ለህወሓት ሙሉ ስልጣን

እንዲሰጠው በግልጽ ይናገራሉ፤

- ከዚህ ጋር በተያያዘ ወታደራዊው አገዛዝ ዛሬ ሲታወጅ የአሜሪካ ድጋፍ ወደ ህወሓት ማዘመሙን በግልጽ የሚያሳይ ይሆናል÷
- በግብጽ የፕሬዚዳንት ሙርሲን አስተዳደር አውርዶ የአሜሪካ ወኪል በሆነው አልሲሲ ሰመተካት በተደረገው ተቃውሞ አደባባይ የወጡ ተቃዋሚ ዜጎችን የአልሲሲ ኃይል ሲጨፈጭፍ ምዕራባውያን በተለይም አሜሪካ የውስጥ ድጋፏን እንደሰጠችው በኢትዮጵያም በቀጣይ የሚከሰተው ይህ እንደሚሆን ጎልጉል የደረሰው መረጃ ያመለክታል
- የኃይል አገዛዝ የትኛውንም መንግሥት እንዳሳጸናው ከታሪክ የማይማረው ህወሓት አሁንም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የበቀል ርምጃውንም ሰመውሰድ ሰይፉን ስሏል÷ የጌቶቹን ቡራኬም እየተቀበለ ነው።

(ተጨማሪ መረጃ እንደደረሰን እናትማለን)

---

**ማሳሰቢያ፤** በተለይ በስም ወይም በድርጅት ስም እስካልተጠቀሰ ድረስ በጎልጉል የድረገጽ ጋዜጣ™ ላይ የሚወጡት ጽሁፎች በሙሉ የጎልጉል የድረገጽ ጋዜጣ™ ንብረት ናቸው። ይህንን ጽሁፍ ስመጠቀም የሚፈልጉ ሁሉ የዚህን ጽሁፍ አስፈንጣሪ (link) ወይም የድረገጻችንን አድራሻ (http://www.goolgule.com/) አብረው መስጠፍ ከጋዜጠኛነት የሚጠበቅና ህጋዊ አሠራር መሆኑን ልናሳስብ እንወዳለን።